## በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1993 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት
# የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
ጥቅምት 1993

# በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1993 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት
# የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
ጥቅምት 1993

## ማ ው ጫ

<u>አርዕስት</u> <u>ገጽ</u>


1. መግቢያ ........ 1

2. የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስ ........ 2
   2.1 የሥነ-ሕዝብና ጤና (DHS) በተመለከተ ........ 2
   2.2 የቫይታል ስታቲስቲክስ በተመለከተ ........ 3
   2.3 የወሣኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓትና የሕዝብ ምዝገባን በተመለከተ ........ 3
   2.4 የሰው ኃይል ስታቲስቲክስን በተመለከተ ........ 4
   2.5 የዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ ........ 5
   2.6 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት ........ 6

3. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ........ 6
   3.1 የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት ........ 6
   3.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት ........ 8
   3.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት ........ 10

4. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ ........ 13
   4.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ ........ 13
   4.2 የካርቶግራፊ ሥራን በተመለከተ ........ 14

5. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ ........ 15

6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና ........ 16
   6.1 የሰው ኃይልን በተመለከተ ........ 16
   6.2 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ ........ 17

7. የበጀት አጠቃቀም ........ 18
   ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም ........ 18
   ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም ........ 19

8. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት ........ 21
   8.1 የዕቃ ግዢን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎች ........ 21
   8.2 ትራንስፓርትና ጥገናን በተመለከተ ........ 21
   8.3 ሕትመት ........ 22
   8.4 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት በተመለከተ ........ 22

9. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ........ 23

# የ1993 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ሪፓርት

## 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት በተገቢው መንገድ ለማፋጠን የሚረዱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች በመሰብሰብ፣ በማጠናቀርና ሪፓርቶች በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች ሲያሰራጭ ቆይቷል፣ በማሠራጨትም ላይ ይገኛል:: በዚህ ዓይነት የተዘጋጁ ሪፓርቶችን መሠረት በማድረግ መንግስት ልዩ ልዩ ፓሊሲዎችን ለመቀረጽ፣ የልማት ዕቅዶችን ለማዘጋጀት፣ እንደዚሁም የተዘጋጁት ዕቅዶች ተግባራዊ ሲሆኑ ውጤታቸውን ለመከታተልና ለመገምገም በየጊዜው ይገለገልባቸዋል:: መ/ቤቱ የሚሰበስባቸውና የሚያጠናቅራቸው የተለያዩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ሁሉንም ዘርፎች የሚዳስሱ በመሆናቸው ሌሎች መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ተመራማሪዎች፣ የከፍተኛ ተቋም ተማሪዎች እንደዚሁም ኢንቬስተሮች... ወዘተ ጥናቶችና ምርምሮች ለማካሄድ ይጠቀሙባቸዋል::

በመሆኑም በ1993 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲችል ባለው የሰው ኃይል፣ ሎጀስቲክስና ከመንግሥት በሚያገኘው ሁለንተናዊ ድጋፍ በመታገዝ ስምንት ልዩ ልዩ ጥናቶችና በ1994 ዓ.ም ለሚካሄደው ብሔራዊ የግብርና ቆጠራ የሚያገለግል የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት የሚያካሂድ ሲሆን በ1992 በጀት ዓመት ለተጀመሩ ስድስት የተለያዩ ጥናቶች የሪፓርት ዝግጅታቸውን ለማጠናቀቅ አቅዶ በመንቀሣቀስ ላይ ይገኛል::

እነዚህም:-

ሀ. ብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም

- I. የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣
- II. የግብርና ናሙና ጥናት፣ ( የመኸርና የበልግ ወቅት፣ የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች ጥናት) ፣
- III. የመንግሥትና የግል ንግድ እርሻዎች ጥናት፣
- IV. የመካከለኛ የትላልቅና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
- V. የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣
- VI. የዕቃዎችና አገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት፣
- VII. የሕፃናት የሥራ ሁኔታ ( Survey of Child Labour ) ጥናት፣

ለ. የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት

ሐ. በዕቅድ ዓመቱ የሚጠናቀቁ የጥናት ሪፓርቶች

I. የ1992 የግብርና ናሙና የበልግ ወቅት ጥናት፣
II. የዲሞግራፊና ጤና ጥናት (DHS)
III. የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ ጥናት፣
IV. የ1992 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
V. የ1992 የኮንስትራክሽን ጥናት፣
VI. የ1992 የማዕድን ቁፋሮ ጥናት ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱትና በዕቅድ ዓመቱ በሚጠኑ ጥናቶች ላይ የባለሥልጣኑ መ/ቤት አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ በማጠናቀቅ በስሩ ባሉት በሃያ ሁለቱም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካይነት የዋና ዋና ጥናቶች የመረጃ መሰብሰብ ሂደት በስፋት ቀጥሏል። በዚሁ መሰረት በ1993 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የተደረገው የሥራ እንቅስቃሴ በዝርዝር በዚህ ሪፓርት ውስጥ የተካተተ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የሰው ኃይል ሁኔታ፣ የፋይናንስ አጠቃቀምና ሌሎች ተግባራትም ተጠቃለው ቀርበዋል። እንደዚሁም በሩብ ዓመቱ ውስጥ በዕቅድ አፈጻጸም ላይ ያጋጠሙ ችግሮች፣ በመ/ቤቱ የተሰጡ መፍትሄዎችና በበላይ አካል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንዲካተቱ ተደርጓል።

## 2. የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በተለያዩ ዘርፎች ያለውን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት እንዲችል የሕዝብና ቤት መረጃን በተመለከተ ከዚህ በፊት ካደረጋቸው ሁለቱ ብሔራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች በተጨማሪ ሕዝብ-ነክ ጥናቶች በማካሄድ ውጤቱን በየጊዜው ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል። በተመሣሣይ ሁኔታ በ1993 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል።

### 2.1 የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናትን (DHS) በተመለከተ

- በ1992 በጀት ዓመት በአገሪቱ የተካሄደውን የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት (DHS) ዋና ዋናዎቹ መረጃዎች የሚይዝ አጭር የቅድሚያ ሪፓርት ( Preliminary Report) ተዘጋጅቷል። ሪፓርቱም የባለሥልጣኑ መ/ቤት ባለሙያዎች ከ MACRO INTERNATIONAL ከተላኩ ኤክስፐርቶች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ሲሆን፣

የቅድሚያ ሪፓርቱን በተመለከተ ለተጠቃሚዎች የግማሽ ቀን የማስታዋወቂያ ሴሚናር በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ወር ላይ ተካሂዷል። በዕለቱም የሪፓርቱ ኮፒ ከመታደሉም በላይ የሪፓርቱ የተለያዩ ምዕራፎች ለሴሚናሩ ታዳሚዎች ቀርበዋል። በሴሚናሩ ላይም ከመንግሥታዊ መ/ቤቶች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከምርምር ተቋማትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።

- የሥነ- ሕዝብና ጤና ጥናት መረጃ ዋናው ሪፓርት ዝግጅት ተጀምሮ፣ የየምዕራፎቹ የመጀመሪያው ረቂቅ (Draft) ድራፍት የተጠናቀቀ ሲሆን ለሪፓርት ዝግጅት የሚያስፈልጉ የኮምፒዩተር ሰንጠረዦችን ማውጣትና አጠቃላይ የሪፓርት ዝግጅቱ የሚካሄደው ደግሞ ከ MACRO INTERNATIONAL ጋር በመተባበር ነው።

## 2.2 የቫይታል ስታቲስቲክስን በተመለከተ

- የ1991/92 የቫይታል ስታቲስቲክስ ሰርቬይና ምዝገባ ጥናት ውጤት በፐብሊኬሽን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ የመረጃ ትንተናና የጽሑፍ ሥራ የመጀመሪያ ደረጃ Draft ተጠናቆ በማዕከሉ ከታየ በኋላ በተሰጠው አስተያየትና እርማት መሠረት ሁለተኛው ረቂቅ (Draft) የመ/ቤቱ የፖሊሲ ኮሚቴ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጎ ጥናቱ የመጨረሻውን የሪፓርት ይዘት በመያዝ ወደ ሕትመት ተልኳል።

- የ1991/92 ዓ.ም የቫይታል ስታቲስቲክስ ሰርቬይና ምዝገባ የተሰበሰቡትን መረጃዎች የማጠናቀር ሥራ የተጀመረ ሲሆን በዚህ መሠረት ከመስክ የተሰበሰቡ ዶክመንቶች ብዛትና ዓይነት ማጣራት ተደርጎ ኤዲቲንግና ኮዲንግ ለሚሠሩ ሠራተኞች ስልጠና መስጠት ተጀምሯል።

## 2.3 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓትና የሕዝብ ምዝገባን በተመለከተ

- ቀደም ሲል በሐረሪ ብሔራዊ ክልልና በድሬዳዋ ካውንስል የቫይታል ስታቲስቲክስ መረጃዎችን በቀጣይነት ለመሰብሰብና ለማጠናቀር በቀረበው የሙያ ድጋፍ ጥያቄ መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቀጣይ ግንኙነት ለማድረግ ተሞክሯል። በተደረጉትም ግንኙነቶች የቫይታል ስታቲስቲክስንም ሆነ የሕዝብ ምዝገባን አግባባዊ (conventional) አሠራሩን እንዲረዱ ተደረጓል። በተለያዩ ቢሮዎች መሃከል ባለው የግንኙነት ክፍተት ምክንያት ሙያዊ ምክሮችን በተገቢው መንገድ ባለመተርጎም ለሚነሱ ጥያቄዎች በተለያየ ጊዜ አስተያየት ተሰጥቷል።

- ስለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስታቲስቲክስ ሥርዓትና የሕዝብ ምዝገባ ቴክኒካዊ አሠራር በኢትዮጵያ እንዴት ማቋቋምና መተግበር እንደሚቻል ጥልቀ ጥናትና ምርምር በማድረግ የአሠራር ስልቶችን ያካተተ ቴክኒካዊ ጽሑፎች ተዘጋጅተዋል:: እንዲሁም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስታቲስቲክስ ሥርዓትን ለማቋቋም የዝግጅት ተግባር የበርካታ ሙያዎች ጥምረት ውጤት ከመሆኑ አኳያ በተለይ በሕግና በአስተዳደር ዘርፍ ከመረጃ ሥርዓቱ የሚገኙ ግላዊና ጥቅል መረጃዎች ላይ ያተኮረና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለመነጋገር መነሻ የሚሆን ጽሑፍ ተዘጋጅቶ ቀርቧል::

- የሥርዓቱን የምዝገባ ሕግ ለማርቀቅ በተደረገው ሙከራ ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍችን ያካተተ የሕግ የመጀመሪያ ረቂቅ ለማዘጋጀት የተሞከረ ሲሆን፣ በተለያዩ ሀገሮች የሥርዓቱን አወቃቀርና አሠራር የሚያሣይ ጽሑፍ የመጀመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል:: እንዲሁም ሥርዓቱን በማዋቀር በሙያና በአተገባበር ተሣታፊ ከሚሆኑ አካላት ጋር ሙያዊ ምክክር ለማድረግ አልፎም የሥራ ግንኙነት ለመፍጠር እየተሞከረ ይገኛል::

- ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት አወቃቀር የቴክኒክና የአሠራር ስልቶችን በመንደፍና ይኸንኑ ዶክመንት ለማድረግ የሚያስችል ሙከራ (experimental) መመሪያዎችና ፎርሞች ዝግጅት በመከናወን ላይ ይገኛል::

## 2.4 የሰው ኃይል ስታቲስቲክስን በተመለከተ

- በ1991 በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጠናው የሰው ኃይል ጥናት አናሊቲካል ሪፓርት ለማዘጋጀት በተደረገው ጥረት የመጀመሪያው ረቂቅ ለመ/ቤቱ ፓሊሲ ኮሚቴ ቀርቦ አስተያየት እየተሰጠበት ሲሆን፣ ይኸንኑም የትንተና ሪፓርት ለማዘጋጀት ልዩ ልዩ ሠንጠረዦች ተዘጋጅተው የትንተናው ሥራ ተከናውኗል:: እንደዚሁም የዚሁ ሪፓርት ዝግጅት ተጠናቆ ለሕትመት ቀርቧል::

- የባለሥልጣኑ መ/ቤት የልጆች የሥራ ሁኔታ ጥናት (Stand Alone Child Labour Survey) እንዲያካሂድ የዓለም የሥራ ድርጅት (ILO) እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ተስማምተው በጠየቁት መሠረት ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስችሉ የተለያዩ ውይይቶች ከተጠቀሱት ድርጅቶች ከፍተኛ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ተካሂደዋል:: በውይይቱም በተደረሰው ውሣኔ መሠረት የጥናቱን በጀት ( በተለያዩ አማራጮች) በማቅረብ እንዲሁም በመጨረሻ የጥናቱን የሥራ ፕሮግራም ( Time table) በማዘጋጀት ረዥም ጊዜ የወሰደ ግንኙነት ተደርጓል:: ምንም እንኳ በዋና ዋና ጉዳዮች ስምምነት

ላይ ቢደረስም ሥራውን ለመጀመር በሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊው የሕግና የአስተዳደር ስምምነት ባለመደረጉ ምክንያት ጥናቱ ሊጀመር አልተቻለም። ቢሆንም የILO ዋናው መ/ቤት በጥቅምት ወር መጀመሪያ ስምምነቱን እንገልጻለሁ ባለው መሠረት መ/ቤቱ ይኸንኑ እየጠበቀ ይገኛል።

2.5 <u>የዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ</u>

- <u>የጤናና አመጋገብ ስታቲስቲክስ</u>

– ለዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆኑ ጤና ነክ መረጃዎችን ከሁለተኛ የመረጃ ምንጭ ( Secondary data source) ለመሰብሰብ የሚያስችሉ 8 ገጽ መጠይቆችን አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የክልል ጤና ቢሮዎችና ለጤና ጥበቃ ሚ/ር ከነሐሴ ወር 1992 ዓ.ም ጀምሮ አሰራጭቷል። የአብዛኛው መጠይቆች ይዘትና ብዛት ካለፈው ጋር ተመሣሣይ ቢሆንም ዘንደሮ አንድ አዲስ መጠይቅ ( በየክልሉ ያሉ መድሃኒት ሻጮችና አቅራቢዎች ብዛት የሚያሣይ) ተዘጋጅቶ እንዲሰራጭ ተደርጓል። ስርጭቱም የተካሄደው ለክልል ጤና ቢሮዎች ነበር። በዚህ በኩል ከ7 ክልሎች ማለትም ኦሮሚያና፣ አማራ፣ ደቡብ ሕዝቦች፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ድሬደዋ እና አዲስ አበባ ጤና ቢሮዎች መረጃውን ሞልተው የላኩ ሲሆን ከሌሎች ክልሎችም መረጃው በቅርቡ እንደሚላክ ይጠበቃል።

- <u>የትምህርት፣ የባህል፣ የስፓርትና የሕግ ስታቲስቲክስ</u>

– የ1992 ዓ.ም የትምህርት መረጃን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ መጠይቆች ተዘጋጅተው ለሁሉም ክልሎች የተላከ ሲሆን ከሁለት ክልሎች መረጃው ተሞልቶ ቢደርስም የሌሎች ክልሎች መረጃ እየተጠበቀ ነው።

– ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ የስፓርት መረጃ በፌዴራል ስፓርት ኮሚሽን ያልወጣ በመሆኑ ከ1990 - 1992 ድረስ ያሉትን የስፓርት መረጃዎች በክልል የስፓርት ኮሚሽን ጽ/ቤቶች ለመሰብሰብ መጠይቆች ተዘጋጅተውና ወደ የክልሉ ተልከው ሁለት ክልሎች መጠይቆቹን ሞልተው ልከዋል።

– የባህል መረጃን በተመለከተ በባህልና ማስታወቂያ ሚ/ር ለማግኘት ተሞክሮ እስካሁን አልተቻለም። በመሆኑም የባህል መረጃ ክፍተትን ለማጥበብ እንዲቻል መጠይቆች ተዘጋጅተው ለክልል ባህል ቢሮዎች ተልከዋል።

– የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስን መረጃ በየዓመቱ ተዘጋጅቶ በሚወጣው ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ለማካተት የ1991 እና የ1992 ዓ.ም የማረሚያ ቤቶችንና የፌዴራል ፖሊስ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲቻል የተለያዩ መጠይቆች ለሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል መ/ቤቶች የተበተኑ ሲሆን፣ መረጃዎቹንም በወቅቱ ለማግኘት እንዲቻል ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛል::

## 2.6. ሌሎች የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ

– ከሁለተኛ ምንጭ ( Secondary Data) የሚገኙ መረጃዎችን ይዘት ለማሻሻል መረጃ ሰጭ ከሆኑ መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሊገኙ የሚችሉ መረጃዎችን ለማጥናት ቅድመ ዝግጅቱ ተጠናቋል::

– ከተለያዩ መረጃ ተጠቃሚዎች የሚቀርቡትን ጥያቄዎች በመቀበል አስፈላጊውን ስታቲስቲካዊ መረጃና ቴክኒካዊ ድጋፍ ተሰጥቷል::

# 3. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ

የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ዘርፈ ብዙና የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለተጠቃሚዎች አዘጋጅቶ ከሚያሰራጫቸው ሪፓርቶች ውስጥ አብዛኞቹ የዚሁ ጥናት ውጤቶች ናቸው:: በመሆኑም በየበጀት ዓመቱ የሚያወጣቸው ሪፓርቶች በዘርፉ ያለውን የመረጃ ፍላጎት እንዲያሟሉ ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ሲሆን፣ በ1993 ዓ.ም በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራምና በግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ሥር ከሚከናወኑት የተለያዩ ጥናቶችና ከ1992 ዓ.ም ለተሸጋገሩ ጥናቶች የሚደረገውን የማጠናቀቅ ተግባር በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል::

## 3.1 የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት

### ሀ. የሰብል ምርት ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

የ1993 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት መረጃዎች ከመስከረም 1 ቀን እስከ መስከረም 30 ቀን 1993 ባለው ጊዜ ተሰብስቦ ተጠናቋል:: ለመረጃ ቅንብር የሚያገለግል የኤዲቲንግና ከዲንግ መመሪያዎችም ተዘጋጅተዋል:: እንደዚሁም የመ/ቤቱ ባለሙያዎች ይህንኑ የሰብል ምርት ትንበያና የግብርና

ናሙና ጥናቶች ከመስክ የሚሰበሰበውን መረጃ ጥራት ለመከታተል ጥናቱ በሚካሄድባቸው ቦታዎች በመዘዋወር የቁጥጥር ተግባር አከናውነዋል፡፡

ለ. <u>የእርሻ መሬት ስፋት መረጃን በተመለከተ</u>

የ1992 ዓ.ም በበልግ ወቅት የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና የቅንብር ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን የጥናቱ ውጤት ሪፓርት ለማዘጋጀት CV በመሥራት ላይ ነው፡፡

ሐ. <u>የእርሻ ሥራን /Farm Management Practices/ በተመለከተ</u>

የ1991 ዓ.ም የበልግ እርሻ ሥራ መረጃ አጠቃላይ ሁኔታ የመረጃ ቅንብሩ ሥራ ተጠናቆ፣ የሪፓርት ዝግጅቱን ለማጠናቀቅ የ CV ውጤቶች ትንተና ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፣ የ1992 ዓ.ም የዋናው መኸር ወቅት እርሻ ሥራ አጠቃላይ ሪፓርት ተጠናቆ በሕትመት ላይ ይገኛል፡፡

መ. <u>መሬት አጠቃቀምን /Land Utilization/ በተመለከተ</u>

የ1992 የመሬት አጠቃቀም ሪፓርት ተጠናቆ በመታተም ላይ ይገኛል፡፡

ሠ. <u>የቤት እንስሳት፣ ዶሮና ንብ የያዙ ቀፎዎች መረጃን በተመለከተ</u>

የ1992 ዓ.ም የቤት እንስሳት መረጃዎች ቅንብርና የሪፓርት ዝግጅቱ ተጠናቆ በመታተም ላይ ይገኛል፡፡

ረ. <u>የግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናትን በተመለከተ</u>

- በ1992 ዓ.ም በተካሄደው የግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናት ላይ በመረጃ መሰብሰቡና ቅንብሩ ወቅት በተገኘው ተሞክሮና ከውጭ መጥተው በነበሩ ኤክስፐርቶች በተሰጠው የማሻሻያ ሃሣቦች መሠረት በዋናው የቆጠራ መጠይቅ፣ መመሪያና ሜቶዶሎጂ ላይ አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎ የቆጠራው ዶክመንቶች በ1993 ዓ.ም ለሚካሄደው የሙከራ ቆጠራ ተዘጋጅቷል፡፡

- በ1992 ዓ.ም ተካሂዶ በነበረው የግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናት ተሰብስበው የነበሩ የከተማ ሙከራ ጥናት መረጃ፣ የበልግ ወቅት የግብርና ጥናት እንዲሁም የመንግሥትና የግል የንግድ እርሻዎች ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ተግባር ተጠናቋል።

- በ1994 በጀት ዓመት ለሚካሄደው ብሔራዊ የግብርና ቆጠራ ቅደመ ዝግጅት ሥራዎች የሚያከናውኑ ስድስት የቴክኒክ ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ የተደረገ ሲሆን፣ የኮሚቴዎቹን ተግባርና ኃላፊነት በማዘጋጀት ለእያንዳንዱ አባል እንዲደርስ ተደርጓል።

ሰ. <u>ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች</u>

- ለ1993 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያና የግብርና ናሙና ጥናት የሚያገለግሉ መጠይቆችና መመሪያዎች በማዘጋጀት ለየቀ/ጽ/ቤቶች ተሰራጭተው እንዲሰራባቸው ተደርጓል።

- መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀው ዓመታዊ መጽሔት ዝግጅት የሚውሉ የግብርናና ሌሎች የግብርና ነክ የሆኑ መረጃዎች ከሌሎች ድርጅቶች የማሰባሰቡ ተግባር በአብዛኛው የተከናወነ ሲሆን፣ የተጨማሪ መ/ቤቶችንም መረጃ ለማግኘት ጥረቱ ቀጥሏል።

## 3.2 <u>የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት ዓለም አቀፍ የአሠራር ዘዴዎችን በመከተል የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናቀር ውጤታቸው ወቅቱን ጠብቆ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያደርጋል። በመሆኑም በዚህ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት በዘርፉ የተከናወኑ ሥራዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 3.2.1 <u>የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክሶችን ሥራ በተመለከተ</u>

ሀ. <u>በከተሞች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት</u>

የ1991 ዓ.ም ከግንቦት እስከ ነሐሴ ድረስ ያለው መረጃ ሪፓርት ተጠናቆ ለሕትመት የተላከ ሲሆን፣ ከመስከረም እስከ ታህሣሥ 1992 ድረስ ያለው

መረጃ ሪፓርቱ ተጠናቆ ለሕትመት ተዘጋጅቷል፡፡ እንደዚሁም የዚሁ ዓመት ከጥር እስከ ሰኔ ድረስ ያለው መረጃ የሪፓርት ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የሐምሌ ወር መረጃ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመካሄድ ላይ ሲሆን የነሐሴ ወር መረጃ ደግሞ የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቋል፡፡

ለ. <u>በገጠር የችርቻሮ ዋጋ ጥናት</u>

ከሐምሌ 1991 እስከ መስከረም 1992 ዓ.ም ድረስ ያለው የመጀመሪያ ሩብ ዓመት መረጃ ሪፓርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ ሲሆን፣ የ1992 ከጥቅምት እስከ ታህሣሥ ድረስ ያለው መረጃ ተቀነባብሮ ለሕትመት ተልኳል፡፡ እንደዚሁም የዚሁ ዓመት ከጥር እስከ ሰኔ ያለው መረጃ ተቀነባብሮ ለሕትመት ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሐምሌ ወር 1992 መረጃ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን የነሐሴ ወር 1992 ዓ.ም መረጃ ደግሞ የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቋል፡፡

ሐ. <u>በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናት</u>

የ1992 ዓ.ም ከመስከረም እስከ የካቲት ወር ድረስ ያለው መረጃ ሪፓርቱ ተጠናቆ ለሕትመት የተላከ ሲሆን የዚሁ ዓመት ከመጋቢት እስከ ሰኔ ድረስ ያለው መረጃ ሪፓርት ተጠናቆ ለሕትመት ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም የሐምሌና የነሐሴ ወራት መረጃዎች የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡

መ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ</u>

- የአገር አቀፍ፣ የገጠርና የከተማ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክሶች

  - የ1992 ዓ.ም እስከ ሐምሌ ድረስ ያሉት ወርሃዊ ኢንዴክሶች ተዘጋጅተውና ታትመው ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ ሲሆን፣ የነሐሴ ወር 1992 ዓ.ም ኢንዴክስ ደግሞ የዳታ ክሊኒግ ሥራ ተጠናቆ ለሕትመት ተዘጋጅቷል፡፡

- የአዲስ አበባ ከተማ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ

- የ1992 ዓ.ም እስከ ነሐሴ ድረስ ያሉት ወርሃዊ ኢንዴክሶች ተጠናቀውና ታትመው ለተጠቃሚ የተሰራጩ ሲሆን የመስከረም ወር 1993 ዓ.ም ኢንዴክስ ደግሞ ተጠናቆ ለሕትመት ተልኳል።

3.2.2 የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት

በ1991 ዓ.ም ሰኔና ሐምሌ ወራት ላይ የተካሄደው አንደኛው ዙር የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት አጠቃላይ የዳታ ክሊኒንግ ሥራው የተጠናቀቀ ሲሆን በ1992 ዓ.ም በጥርና በየካቲት ወራት የተካሄደው የሁለተኛው ዙር የቤተሰብ ገቢ፣ፍጆታና ወጪ ጥናት ደግሞ የዳታ ክሊኒንግ ሥራው 70 በመቶ ተጠናቋል።

3.2.3 የኢኮኖሚና የማህበራዊ ደህንነት ጥናት

በ1992 ዓ.ም ጥርና የካቲት ወራት ላይ የተካሄደው የኢኮኖሚና የማህበራዊ ደህንነት ጥናት የዳታ ኢንትሪ ሥራና የዳታ ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቋል።

3.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት

3.3.1. የኢንዱስትሪ፣ የኮንስትራክሽንና የማዕድን ቁፋሮ ጥናት

ሀ. የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት

የ1991 ዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪን በተመለከተ በመጋቢት ወር 1992 በተካሄደው ጥናት የተሰበሰበው መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ እንዲሁም የዳታ ኢንትሪ ሥራዎች ተጠናቀው የዳታ ክሊኒንግና የታቡሌሽን ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው።

ለ. የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ ጥናት

የ1991 ዓ.ም የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪን በተመለከተ በመጋቢት ወር 1992 ዓ.ም በተካሄደው ጥናት የተሰበሰበው መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ በዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መጽሔት ውስጥ ለማካተት በሠንጠረዥ መልክ በመጠናቀር ላይ ይገኛል።

ሐ. <u>የኮንስትራክሽን አጠቃላይ ቆጠራን በተመለከተ</u>

የ1991 ዓ.ም የኮንስትራክሽን ጥናትን በተመለከተ በሚያዚያ ወር 1992 ዓ.ም በተካሄደው ጥናት ላይ የተሰበሰበውን የዘርፉ ጥናት መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ተጠናቆ ዳታ ኢንትሪ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

መ. <u>የማዕድን ቁፋሮ ጥናት</u>

የ1991 ዓ.ም ዘርፉን በተመለከተ በግንቦት ወር 1992 ዓ.ም በተካሄደው ጥናት የተሰበሰበው መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ተጠናቋል፡፡

ሠ. <u>ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች</u>

ለዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ( STATISTICAL ABSTRACT) ዝግጅት የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃና የማዕድን ምርት መረጃዎች በመቀነባበር ላይ ናቸው፡፡

3.3.2 <u>የንግድ፣ የትራንስፓርት፣ መገናኛና ፋይናንስ መረጃ</u>

- የ1990/91 ዓ.ም የትራንስፓርትና መገናኛ መጽሔት የመረጃ ቅንብር ሥራ ተጠናቆ ለሕትመት ተልኳል፡፡
- የውጭ ንግድ የመጀመሪያው መጽሔት እ.ኤ.አ የ1997 - 1999 ያለውን የውጭ ንግድ መረጃ የያዘ ሪፓርት ተቀነባብሮ ለሕትመት የተላከ ሲሆን፣ የውጭ ንግድ ኢንዴክስ መጽሔት ደግሞ የመረጃ ቅንብርና የጽሑፍ ሥራዎች በመሠራት ላይ ይገኛል፡፡
- ለዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ( STATISTICAL ABSTRACT) የሚያስፈልጉ መረጃዎች በመሰባሰብ ላይ ናቸው፡፡
- በተጨማሪም በሁሉም ዘርፎች እያደገ የመጣውን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት ለመረጃ ተጠቃሚዎች መረጃ የመስጠትና አጠቃቀሙንም የማስረዳት ሥራ ተከናውኗል፡፡

## 1993 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የጥናቶች የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

ሠንጠረዥ 1

| ተ.ቁ | የጥናቱ ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1992 በጀት ዓመት መጨረሻ | የ1993 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
| 1 | **የግብርና ጥናት** | | | | | |
| 1.1 | የ1993 የግብርና ሰብል ትንበያ | አዲስ | 11 | 52 | 52 | 100 |
| 1.2 | የ1993 የግብርና ናሙና ጥናት | አዲስ | 11 | 17 | 17 | 100 |
| 1.3 | የ1992 የግብርና ናሙና ጥናት | ነባር | 90 | 10 | 5 | 50 |
| 2 | **የዋጋዎች ጥናት** | | | | | |
| 2.1 | የ1992 የአምራቾች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ | ነባር | 93 | 7 | 7 | 100 |
| 2.2 | የ1992 የአምራቾች የችርቻሮ ዋጋ በገጠር | ነባር | 93 | 7 | 7 | 100 |
| 2.3 | የ1993 የአምራቾች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት | አዲስ | 15 | 4 | 4 | 100 |
| 3 | **የ1992 የዲሞግራፊና ጤና ጥናት** | ነባር | 78 | 7 | 7 | 100 |
| 4 | **የ1992 የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናት** | ነባር | 72 | 18 | 15 | 83 |
| 5 | **የ1992 የኮንስትራክሽን ጥናት** | ነባር | 65 | 10 | 10 | 100 |
| 6 | **የ1992 የማዕድን ቁፋሮ ጥናት** | ነባር | 65 | 10 | 10 | 100 |
| 7 | **ዋጋዎች ኢንዴክስ ሥራ** | | | | | |
| 7.1 | በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሠራው የዋጋ ኢንዴክስ በከተማ | አዲስ | - | 33 | 30 | 91 |
| 7.2 | የአዲስ አበባ የዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | - | 25 | 25 | 100 |

## 4. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ

### 4.1 የሰርቬይ ዲዛይን ሥራን በተመለከተ

በየበጀት ዓመቱ መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው የተለያዩ የስታቲስቲክስ ጥናቶች የሚያገለግሉ የአሠራር ዘዴዎችንና የአፈፃፀም መመሪያዎችን እንደዚሁም ለጥናቶቹ የሚያገለግሉ መጠይቆችና ቅጾች ጥራቱ፣ ብቃትና ወካይነታቸውን በማረጋገጥ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የሚደረግ ሲሆን በ1993 በጀት ዓመትም ተመሣሣይ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው። በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሚከተሉት ሥራዎች ተከናውነዋል።

#### ሀ. የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም

- በ1992 ዓ.ም ለተካሄዱት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናቶች፣ የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናቶች፣ የበልግ የግብርና ናሙና ጥናት ማባዣ (weight) ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተሰጥቷል።

- የ1993 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት አካል ለሆነው የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት የሚሆን ማባዣ ለማዘጋጀት አስፈላጊው ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን መረጃው ከመስክ እንደመጣ ማባዣው ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ይሰጣል። እንደዚሁም በ1993 ለሚካሄዱ የናሙና ጥናቶች የአካባቢ መለያ ኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተሰራጭተዋል።

#### ለ. የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት

- ለግብርና ናሙና ጥናት በተመረጠው ዲዛይን ላይ ተጨማሪ ፍተሻ (investigation) ለማካሄድ አንዳንድ ውሣኔ በሚፈልጉ የሳምፕሊንግ ፕላን ነጥቦች ላይ የክፍሉ ሠራተኞች ከUSAID ከመጣው አማካሪ ጋር በመሆን ሠርተዋል።

- ቀደም ሲል ለግብርና ናሙና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ለቤተሰቦች መመዝገቢያ በተዘጋጀው መመሪያ ላይ በመመርኮዝ ጽንሰ ሀሣቡን ሳይለቅ ሌላ አዲስ አሠራርና ቀለል ያለ የቤተሰቦች መመዝገቢያና የናሙና ቤተሰቦች አመራረጥ መመሪያ ተዘጋጅቶ የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል። እንዲሁም ጥናቶቹ

በሚካሄድባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በመገኘት ለመስክ ሥራ ተቆጣጣሪዎችና ለመረጃ ሰብሳቢዎች አስፈላጊውን ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ የመስክም ማምገግ ተካሂዷል፡፡

ሐ. የማዕድን ቁፋሮ ጥናት

ለዚህ ጥናት ማባባር ለማዘጋጀት አስፈላጊው ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን ጥናቱን ከሚመለከተው መምሪያ የሚጠበቀው አስፈላጊ ግብዓት እንደመጣ ማባባሪውን አዘጋጅቶ ለክፍሉ ለመስጠት ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡

## 4.2 የካርቶግራፊ ሥራን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት የተለያዩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲቻል ለናሙና መረጣ እንደፍሬም (Sampling Frame ) የሚያገለግሉ የቆጠራ ቦታ ካርታዎች፣ የስታቲስቲክስ መረጃ ውጤቶች የሚያመለክቱ ልዩ ልዩ ግራፎች፣ ቻርቶች እና ሥዕላዊ መግለጫዎች እንደዚሁም ለተለያዩ ተግባራት የሚውሉ ቲማቲክ ካርታዎች፣ ለስታቲስቲክስ ጥናት የሚያስፈልጉ የአስተዳደር ክፍሎችን፣ የቦታ ስሞችን፣ አዳዲስ ከተሞችንና የገጠር አሰፋፈር ሁኔታ (Settlement Pattern ) ለውጥ ለመከታተል የካርታዎችን ወቅታዊነት በመጠበቅ አስተካክሎ ያዘጋጃል፡፡ በመሆኑም በ1993 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ላይ የሚከተሉትን ሥራዎች አከናውኗል፡፡ ይኸውም፡-

- በ1:2,000,000 መስፈርት የኢትዮጵያ ካርታ በክልልና በዞን እንዲሁም ዋና ዋና የመኪና መንገዶችንና የከተሞችን አቀማመጥ የሚያሳይ ካርታ በካርታ ዝግጅት ክፍል በእንግሊዝኛ ተዘጋጅቷል፡፡

- በ1:250,000 መስፈርት ካርታ ላይ የሎንግቲውድና ላቲቲውድ መስመሮች በሁለት ዞኖች ካርታ ላይ ተሠምረዋል፡፡

- በ1:250,000 በ3 ዞኖች ካርታ ላይ የከፍታ /Elevation/ ከንቱሮች ሥራ ተጠናቋል፡፡

- የጂዎግራፊና የመንደር ስሞች ዝርዝር ለማዘጋጀት በ22 ዞኖች የተሰራ ሲሆን በተመሣሣይ ሁኔታ የ7 ዞኖች ሥራም በመካሄድ ላይ ነው።

- የደቡብ ሕዝቦችና የአማራ ብሔራዊ ክልሎች በአዲሱ የገበሬ ማኀበራት ቀንጆት መሠረት በአዲስ ኮድ ተሰርተዋል።

- ሙያዊ እገዛና ምክር ለጠየቁ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ከአገልግሎቱ አስፈላጊው ምክር ተሰጥቷቸዋል።

5. <u>ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየዓመቱ እያዘጋጀ የሚያወጣውንና የአገሪቷን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ-ነክ ሁኔታዎችን የሚገልጹ መረጃዎች ለሚይዘው ለዚህ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆን መረጃ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች የመሰብሰብ ተግባር በመጀመሩ መረጃ የሚሞላባቸው መጠይቆች ለተለያዩ ክልሎች ተልከው መረጃዎች ተሞልተው በመመለስ ላይ ሲሆኑ ቀሪዎቹም እየተጠበቁ ናቸው።

መጽሔቱ በሚዘጋጅበት ወቅት ተጠቃለው ከሚካተቱት መረጃዎች ውስጥ፡-

- የሥነ ሕዝብ መረጃዎች፣
- የግብርና መረጃዎች፣
- የማዕድንና ምርት መረጃዎች፣
- የማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢነርጂ መረጃዎች፣
- የሀገር ሀብት መረጃዎች፣
- የመንግሥት ገንዘብ /Public Finance/ መረጃዎች፣
- የባንክ ሥራዎችና የአከፋፈል ሚዛን መረጃዎች፣
- የጤናና የትምህርት መረጃዎች፣
- የሕግና ደንብ መረጃዎች፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች፣
- የሕንፃ ሥራ መረጃዎች፣
- የውጭ አገር ንግድ መረጃዎች፣
- የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች፣...ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

# 6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና

## 6.1 የሰው ኃይልን በተመለከተ

በ1993 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,465 ቋሚና 1,811 የኮንትራት በጠቅላላው 3,276 ሠራተኞች ነበሩ ። ከነዚህ የሰው ኃይል ውስጥ 13 ሠራተኞች በራሳቸው ፈቃድ ሥራቸውን የለቀቁ፣ 8 ሠራተኞች በሞት የተለዩ እንደዚሁም 1 ሠራተኛ በጡረታ የተገለሉ ሲሆን የ 26 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር ተፈጽሟል። በሌላ በኩል በዚህ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ውስጥ 184 ጀማሪ መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 23 የፐርሰኔል ሠራተኞች እንደዚሁም 7 ሹፌሮች በድምሩ 214 አዲስ የኮንትራት ሠራተኞች ሲቀጠሩ 74 ሠራተኞች ከሥራ ተሰናብተዋል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት 3,420 ሲሆን ከእነዚህ መሀል 1,469 ቋሚና 1,951 ደግሞ ኮንትራት ሠራተኞች ናቸው። በሩብ ዓመቱ መጨረሻ ያለው የመ/ቤቱ ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት በሠንጠረዥ 2 ቀርቧል።

<u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሰው ኃይል ሁኔታ</u>

<u>ሠንጠረዥ 2</u>

| ተራ ቁጥር | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,465 | 1,811 | 3,276 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 26 | 214 | 240 |
| 3 | በጡረታ የተገለሉ | (1) | - | (1) |
| 4 | ሥራ የለቀቁ | (13) | (74) | (87) |
| 5 | በሞት የተለዩ | (8) | - | (8) |
| ድምር | | 1,469 | 1,951 | 3,420 |

የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በሙያ ሲተነተን 137 ባለሙያዎች፣ 944 መለስተኛ ባለሙያዎች እና 388 የአስተዳደር፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው። የእነዚህ ሠራተኞች ብዛት በፆታ ሲለዩ ደግሞ 1,147 ወንዶች /78.2 በመቶ/ ሲሆን 320 ሴቶች /21.8 በመቶ/ ናቸው።

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ሠራተኞች ሁኔታ በሥራ መደብ

ሠንጠረዥ 3

| | ቋሚ | | | | ኮንትራት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፆታ | ፕሮፌ ሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ፕሮፌ ሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ጠቅላላ ድምር |
| ወንድ | 122 | 860 | 167 | 1,149 | 33 | 1,421 | 167 | 1,621 | 2,770 |
| ሴት | 15 | 84 | 221 | 320 | 4 | 324 | 2 | 330 | 650 |
| ድምር | 137 | 944 | 388 | 1,469 | 37 | 1,745 | 169 | 1,951 | 3,420 |

6.2 የሰው ኃይል ስልጠናን በተመለከተ

በየጊዜው እያደገ የሚመጣውን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት እንዲቻል በስታቲስቲክስ መረጃ ዝግጅትና በሌሎች ተመሣሣይ ሥራዎች ብቁ ባለሙያ ለማግኘትና ያላቸውንም ዕውቀት ከፍ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሰው ኃይል ስልጠናን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል።

ሀ. በ1993 ዓ.ም ለሚካሄደው በገጠር የተቀናጀ ሰርቬይ የአሰልጣኞች ሥልጠና ከሐምሌ 27 እስከ ነሐሴ 10 ቀን 1992 ዓ.ም በዋናው መ/ቤት የተካሄደ ሲሆን በሥልጠናውም ላይ ከተለያዩ መምሪያዎች 48 ባለሙያዎች፣ እንዲሁም ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደግሞ 84 በጠቅላላው 132 ሰልጣኞች ተካፋይ ሆነዋል። በተመሣሣይ ሁኔታ ለመስክ ሠራተኞች በ22ቱም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከነሐሴ 15 እስከ 30 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ ሥልጠና ተሰጥቷል።

ለ. ባለፈው ዓመት የተካሄደውን የግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናት ውጤት ይበልጥ የተሟላ ለማድረግ በዚህ ዓመትም ከአማራ፣ ከኦሮሚያና ከደቡብ ሕዝቦች በናሙና በተመረጡ ሦስት ወረዳዎች ( ቀወት፣ ሳሲጋና የም ልዩ ወረዳ) ውስጥ ከእያንዳንዱ ወረዳ 25 በጠቅላላው 75 የቆጠራ ቦታዎች በጥናቱ ስለሚሸፈኑ ለዚሁ ጥናት ለተቀጠሩ መረጃ ሰብሳቢዎችና ለመስክ ሥራ ተቆጣጣሪዎች ከነሐሴ 10 እስከ ጳጉሜ 5 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ ሥልጠና ተሰጥቷል።

ሐ. በዓለም የሥራ ድርጅት (ILO) የሥልጠና ማዕከል ሁለት የመ/ቤቱ ባለሙያ ጣሊያን ቱሪን በመሄድ አንድ ወር የፈጀ ስልጠና አግኝተው ተመልሰዋል።

መ. የመ/ቤቱ የባለሙያዎች ብቃት ከፍ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ከአገር ውስጥና ከአገር ውጭም በየተለያየ ወቅት ሥልጠና ሲሰጥ ቆይቷል:: ይህንኑ በማጠናከር በ1992 ስድስት ሠራተኞች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጀምረውት የነበረው የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ሦስቱ ሲያጠናቅቁ የቀሩት ሦስቱ ደግሞ እየተከታተሉ ናቸው:: በተመሣሣይ ሁኔታ በ1993 የትምህርት ዘመን አራት ሠራተኞች ማለትም አንዱ በዲሞግራፊ ሦስቱ ደግሞ በስታቲስቲክስ የማስተርስ ዲግሪ ፕሮግራም ለመከታተል አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብተዋል:: በተጨማሪም ሁለት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በዲሞግራፊ የማስተርስ ዲግሪ ትምህርታቸውን ለመከታተል በአክራ ጋና ዩኒቨርስቲ በሚገኘው ( Regional Institute for Population Studies) ወደሚባለው ተቋም ሄደዋል:: በሌላ በኩል የድሕረ ምረቃ ፕሮግራም ሊከታተሉ ወደ ቦትስዋና ሄደው የነበሩት አምስት ሠራተኞች ትምህርታቸውን አጠናቀው የተመለሱ ሲሆን ሌሎች 6 ሠራተኞች ከታንዛኒያ ትምህርታቸውን ተከታትለው ሠርተፊኬት በማግኘት ተመለሰዋል:: ከዚህም በተጨማሪ ሁለት ሠራተኞች በጀርመንና በጃፓን የአጭር ጊዜ ሥልጠና ተከታትለው ተመልሰዋል::

## 7. የበጀት አጠቃቀም

ለ1993 በጀት ዓመት ለአጠቃላይ የባለሥልጣኑ መ/ቤት የመደበኛና የካፒታል ወጪ ብር 62,056,876 በዕቅድ የተያዘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ብር 11,764,000 ( የ1992 ዓ.ም በጀትን እንደመነሻ በመያዝ)፣ ለካፒታል በጀት ደግሞ ብር 50,292,876 ተፈቅዷል:: ከተፈቀደው በጀት ውስጥ 18.96% ለመደበኛ በጀት የተያዘ ሲሆን 81.04% ደግሞ ለካፒታል በጀት የተመደበ ነው::

### ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

ጠቅላላ የተፈቀደው በጀት በሚከተለው የወጪ አርዕስቶች የተከፋፈለ ነው:: ይኸውም:-

- ለደመወዝ ..................ብር 10,710,200.00
- ለውሎ አበል ............... " 41,300.00
- ለሥራ ማስኬጃ ............. " 1,012,500.00 የተያዘ ነው

በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ሥራ ላይ የዋለው መጠን:-

- ለደመወዝ ክፍያ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 2,283,437.36 ሲሆን ከሐምሌ 1 ቀን 1992 እስከ መስከረም 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ብር 2,283,436.91 ወጪ የተደረገ ሲሆን አጠቃቀሙም መቶ በመቶ ነው።

- ለውሎ አበል ክፍያ ከተፈቀደው ብር 41,300.00 ውስጥ በመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 3,441.00 ሲሆን ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 1,350.30 ( 39.24%) ነው።

- ለሥራ ማስኬጃ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ላለፉት ሦስት ወራት ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 65,350.00 ሲሆን ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 112,784.24 ነው። አፈጻጸሙም ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 172.58 በመቶ ነው።

ለ1993 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ማለትም ከሐምሌ 1 ቀን 1992 እስከ መስከረም 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ለመደበኛ በጀት ወጪ የሆነው ብር 2,397,571.45 በእጅ ከገባው ብር 2,352,228.36 ጋር ሲነፃፀር 101.93 በመቶ ነው።

ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1993 ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮግራሞች ብር 50,292,876.00 የተፈቀደ ሲሆን ይህም ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 23,121,151.00፣ ለግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ፕሮግራም ደግሞ ብር 27,171,725 የተፈቀደ ነው።

ከሐምሌ 1 ቀን 1992 እስከ መስከረም 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ለተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 5,660,700.00 ወጪ የተደረገ ሲሆን ለግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ደግሞ ብር 234,950.00 ወጪ ሆኖ በሥራ ላይ ውሏል። ለሁለቱ ፕሮግራሞች በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በጠቅላላ ወጪ የሆነው ብር 5,895,650.00 ነው።

የመደበኛና የካፒታል በጀት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ብር 8,725,204.56 ተጠይቆ በእጅ የገባ ሲሆን ብር 8,293,221.45 ደግሞ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። ወጪ የተደረገው በእጅ ከገባው ጋር ሲነፃፀርም 95.04 በመቶ ይሆናል። አሃዛዊ መረጃውም በሠንጠረዥ 4 ላይ ተመልክቷል።

<u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የ1993 ዓ.ም በጀት አጠቃቀም</u>

<u>ሠንጠረዥ 4</u>

| ተራ ቁጥር | የበጀት አጠቃቀም | ለ1993 በጀት ዓመት ከመንግስት ግምጃ ቤት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነ | በእጅ ከገባው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት /በ03 እና በ04/ |
|---|---|---|---|---|---|
| 00 | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| 1 | <u>ለመደበኛ በጀት</u> | 11,764,000.00 | 2,352,228.36 | 2,397,571.45 | /45,343.09/ |
| 1.1 | ለደመወዝ | 10,710,200.00 | 2,283,437.36 | 2,283,436.91 | 0.42 |
| 1.2 | ለውሎ አበል | 41,300.00 | 3,441.00 | 1,350.30 | 2,090.70 |
| 1.3 | ለሥራ ማስኬጃ | 1,012,500.00 | 65,350.00 | 112,784.24 | /47,434.24/ |
| 2 | <u>ለካፒታል በጀት</u> | 50,292,876.00 | 6,372,976.20 | 5,895,650.00 | 477,326.20 |
| 2.1 | ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም | 23,121,151.00 | 5,212,628.20 | 5,660,700.00 | /448,071.80/ |
| 2.2 | ለግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናትና ሌሎች የዝግጅት ሥራዎች | 27,171,725.00 | 1,160,348.00 | 234,950.00 | 925,398.00 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **62,056,876.00** | **8,725,204.50** | **8,293,221.40** | **863,966.20** |

## 8. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት

የባለሥልጣኑ መ/ቤት የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች በበጀት ዓመቱ ለማካሄዱት ጥናቶች እገዛ የሚያደርጉ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ እነዚህም፡-

### 8.1 የዕቃ ግዥን በተመለከተ

ከሐምሌ 1 ቀን 1992 እስከ መስከረም 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶች አገልግሎት እንዲውሉ ብር 5,997,897.87 ወጪ ተደርጎ የተለያዩ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዢ ተፈጽሟል፡፡ ዝርዝሩም በሚከተለው ሠንረጠዥ ቀርቧል፡፡

በ1993 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የተፈፀመ ግዢ

ሠንጠረዥ 5

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ወጪ /በብር/ | ሣ |
|---|---|---|---|
| 1 | የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎች | 57,366 | 23 |
| 2 | የጽሕፈት መሣሪያ | 113,314 | 80 |
| 3 | የቢሮ ዕቃዎች | 17,692 | 75 |
| 4 | ለሕንፃና የኤሌክትሪክ ዕቃዎች | 120,009 | 35 |
| 5 | ነዳጅና ቅባት | 297,843 | 20 |
| 6 | ጀንጥኛ ኮምፓስና ሜትር( ለግብርና ቆጠራ) | 5,348,480 | 00 |
| 7 | ልዩ ልዩ | 43,191 | 54 |
| | ድምር | 5,997,897 | 87 |

### 8.2 ትራንስፖርትና ጥገና

- በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት ተመድበው የሰርቪስ አገልግሎት ከሚሰጡት 14 አውቶሞቢሎች በተጨማሪ 178 የመስክ መኪናዎች በ22ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

- ለ53 መኪናዎች ከባድና መለስተኛ ጥገናዎች በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች አማካይነት ተከናውነዋል። ለዚህም ብር 522,485.63 ወጪ ተደርጓል።

- 12 መኪናዎች በመድን ድርጅት አማካይነት እንደጉዳታቸው መጠን አስፈላጊው ጥገና ተደርጎላቸው ለአገልግሎት ብቁ ሆነዋል።

- 10 የመ/ቤቱ መኪናዎች ለምርጫ በርድና አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን በትውስት ተሰጥተው ለሁለት ወራት አገልግሎት ሰጥተዋል።

8.3. <u>ሕትመት</u>

በ1993 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 39 ዓይነት የተለያዩ የሕትመት ሥራዎች (በጥራዝና በብትን ፎርሞች) ተከናውነዋል። አጠቃላይ የታተሙት ጥራዞች ብዛት 48,353 ሲሆን የገጻቸው ብዛት ደግሞ 319,729 ነው።

8.4 <u>ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት</u>

ሀ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት የማኔጅመንት አባላት፣ ከልዩ ልዩ መምሪያዎችና አገልግሎቶች የተውጣጡ ባለሙያዎችና የሃያ ሁለቱም ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች በተገኙበት ከሐምሌ 26-27 ቀን 1992 ዓ.ም በግዮን ሆቴል አዳራሽ ስብሰባ ተካሂዷል። በስብሰባው ላይ በ1992 በጀት ዓመት ስለተካሄዱ ጥናቶች፣ በአሠራር ላይ ስለታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖችና ስለአጋጠሙ ችግሮች፣ ለችግሮቹ ስለተሰጡ የመፍትሔ ሃሣቦች እንደዚሁም በ1993 ዓ.ም መ/ቤቱ በሚያካሂዳቸው የተለያዩ ጥናቶች የመረጃ ጥራትን ለማሻሻልና የጥናቶቹን ውጤት በወቅቱ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ለማድረግ በሚያስችሉ ሁኔታዎች ሰፋ ያለ ውይይት ተካሂዷል።

ለ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከአምስት የተለያዩ መ/ቤቶች በቀረበለት የካርታ ሽያጭ ጥያቄ መሠረት የ9 ወረዳ ካርታዎቹን በብር 324 ( ሦስት መቶ ሃያ አራት ብር) ኮፒ ተደርጎ ተሸጦላቸዋል።

ሐ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየዓመቱ ከሚያካሂዳቸው ጥናቶች የሚዘጋጁ ሪፓርቶችን ለተጠቃሚዎች በነፃና በሽያጭ የሚያሰራጭ ሲሆን በዚህ ሩብ ዓመትም 3,496 ሪፓርቶችን ለሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ለመንግሥትና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች

እንዲሁም ለግለሰቦች አሰራጭቷል:: ከዚህ ውስጥ 2,630 በነፃ የታደለ ሲሆን ቀሪዎቹ 866 ሪፓርቶች ደግሞ በብር 18,980.35 በሽያጭ ተሰራጭተዋል::

## 9. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተሰጡ መፍትሄዎች

ሀ. የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ገጽታዎች የሚያመለክቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ሰብስቦና አጠናቅሮ ለመረጃ ተጠቃሚዎች በወቅቱ የማቅረቡ ተግባር የባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊነት ነው:: ይህንን መወጣት ይቻል ዘንድ በየዘርፉ የሰለጠነና ልምድ ያካበተ ባለሙያ መኖር ያስፈልጋል:: ነገር ግን የመ/ቤቱ ነባርና የሰለጠኑ ሠራተኞች ለተሻለ ደመወዝ ወደሌላ መ/ቤት እንዳይሄዱ ለማቆየትና በተለያየ ምክንያቶች ማለትም በሞት፣ በጡረታ... ወዘተ በተለዩት ምትክ ተጨማሪ አዳዲስ ባለሙያዎች ከገበያ ፈልጎ ለመቅጠር እንዲቻል ለመ/ቤቱ ልዩ የምደባ ስኬል እንዲፈቀድና ተግባራዊ እንዲሆን ያስፈልጋል:: ከዚህም ሌላ ለመ/ቤቱ ተጨማሪ የሰው ኃይል ለመቅጠር የሥራ መደብ መፍጠርና በመዋቅር ያለውም መደብ የፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እንደገና reclassify ማድረግ ይኖርበታል::

ለ. መ/ቤቱ በተለያየ ዘርፍ ለሚያካሄዳቸው ጥናቶች እገዛ እንዲያደርጉ ከውጭ አገር በእርዳታ የተገኙ የፋክስ ማሽኖች አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ከቴሌኮሙኒኬሽን ፈቃድ ተጠይቆ እስከ አሁን አዋንታዊ ምላሽ አልተገኘም:: እርዳታ ሰጪው ድርጅት ማሽኖቹ ለሥራ አስፈላጊነታቸውን አምኖበት የሰጠ በመሆኑና መ/ቤታችንም በአገሪቱ ያሉት የሀያ ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች ሥራ ለማቀላጠፍ ከመርዳቱም ሌላ የሚጠኑ ጥናቶች ጥራትም እንደሚያሻሽለው ይታመናል:: በመሆኑም የተጠየቁት የፋክስ ማሽኖች ትኩረት በመስጠት መፈቀድ ይኖርበታል::

ሐ. እያደገ የመጣው የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት እንዲቻል በየወቅቱ ቁጥራቸው በዛ ያለ ባለሙያዎች ስለሚቀጠሩ እንደዚሁም ከዚህ በፊት የተቀጠሩትም ለሥራቸው ምቹ የሆነ ቢሮ ለማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ ስለመጣ ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶች ለሥራ አመቺ የሆነ ቢሮ ለማግኘት መፍትሔ መሻት ያስፈልጋል::

መ. ቁጥሩ በዛ ያለው የሃያ ሁለቱም ቅ/ጽ/ቤት የቋሚ ሠራተኞች ደመወዝ በዋናው መ/ቤት መክፈሉ ለአሰራር አስቸጋሪ መሆኑን በሂደት ለመገንዘብ ተችሏል:: የችግሩ አሳሳቢነት ግንዛቤ እንዲያገኝ ተደርጎ ገንዘብ ሚ/ር ለተጠቀሱት ሠራተኞች ደመወዝ በቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ቀጥታ ክፍያ የሚያገኙበት ፔሮል በተናጠል ማዘጋጀት ይኖርበታል::

ሠ. ባለፉት ዓመታት አብዛኛው የቅ/ጽ/ቤቶች አስተዳደር ነክ ጉዳዮች የሚከናወነው በዋናው መ/ቤት በኩል ነበር፤ ይሁን እንጂ ችግሩን ለማቃለል ለቅ/ጽ/ቤቶች የአስተዳደርና የፐርሰኔል ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞች እንዲቀጠሩ ተደጋጋሚ ጥያቄ ለፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ ኮሚሽኑም ሥራው ጊዜ የማይሰጥ መሆኑን ስላመነበት የፐርሰኔል ሰራተኞች በኮንትራት እንዲቀጠሩ ፈቅዷል፡፡ ሆኖም ለሌሎች የሥራ መደቦች የተጠየቀውን የመደብ መታወቂያ ቁጥር ኮሚሽኑ ባለመፍቀዱ ችግሩ ስላልተቃለለ አሁንም መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል፡፡